

# አጣሪዎች/ቴስተሮች ይፈለጋሉ

### ከሚድ-ሚኔሶታ የህግ ድጋፍ (Mid-Minnesota Legal Aid) ጋር ሆነው አድልዎን ይዋጉ

**አጣሪ/ቴስተር ምንድን ነው?**
የፌይር ሃውሲንግ አጣሪዎች/ቴስተሮች የኪራይ ቤቶችን በመደወል ወይም በአካል በመጎብኘት ፍላጎትን በመግለጽ እንደ የወደፊት ተከራዮች ሆነው ያገለግላሉ። በሚድ-ሚኔሶታ የህግ ድጋፍ ስለቤቶች አድልዎ ህግ ፕሮጀክት ያላቸውን ልምድ በተመለከተ ዝርዝር ዘገባዎችን ያጠናቅራሉ። የቴስተር ሪፖርቶች አጣሪዎቹ በማንነታቸው ላይ ተመስርተው በተለየ ሁኔታ መስተናገዳቸውን ለማየት ይነጻጸራል።

**ለምን ይጣራል?**
የመኖሪያ ቤት መድልዎ ተጨባጭ ችግር ቢሆንም ግን፣ ማረጋገጥ ከባድ ሊሆን ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ፣ "ለሆነ ዝርያ ሰዎች አናከራይም" እንደሚለው ግልጽ መድልዎ አይደለም። የመንግስት ኤጀንሲዎች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች የመድልዎ ዘገባዎችን ለመመርመር አጣሪዎችን ይጠቀማሉ። የማጣራት ውጤቶች በሺዎች የሚቆጠሩ የተሳካላቸው የኤጀንሲ ቅሬታዎች፣ ክሶች እና ሌሎች የቤት መድሎዎችን ለማስወገድ ለተወሰዱ እርምጃዎች እረድተዋል። አንድ አጣሪዎችን በመጠቀም የተሳካ ጉዳይ እስከ ዩኤስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ አምርቷል!

**የእርስዎን እርዳታ እንፈልጋለን!**
የማጣራት ፕሮግራሞች ብዝሃነት ያስፈልጋቸዋል። የተለያየ ዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ችሎታ፣ ዕድሜ እና ጾታ ያላቸው ሰዎች ያስፈልጉናል። አጣሪዎች ስልጠና የሚያገኙ ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ ማጣራት መጠነኛ ክፍያ ያገኛሉ። አጣሪዎች እምነት የሚጣልባቸው እና ከማጣራት በኋላ ሪፖርትን ማዘጋጀት መቻል አለባቸው።

**እርስዎ ለምን አጣሪ መሆን አለብዎ?**
አጣሪዎች የመኖሪያ ቤት አድልዎ ለመዋጋት ይረዳሉ። ሰዎች በመረጡት ቦታ እንዲኖሩ ይረዷቸዋል። ስራዎ የቤት አከራዮች እና የንብረት ባለቤቶች ህጉን እንዲያከብሩ ይረዳል።


አጣሪ ለመሆን ፍላጎት ካሎት ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ ያነጋግሩን፡-
**Halley Norman የፌይር ሃውሲንግ ምርመራ እና ግኑኙነት አስተባባሪ**
fairhousingtesting@mylegalaid.org 612-746-3752